# አይደለም ጎሳ ማንነቴ

በእምነቴ
ዋጋ ሆነ ሞቴ
ይገርማል ይደንቃል
በእውኔም ሆነ በሕልሜ ሳስብ ሳንሰላስል
በዚያ የፍቅር መንደር
ተወልጀ ሳድግ
ከዛፉ ከወፉ
መልስ ይፈልጉ
እንቆቅልሽ፣
እኔ ምን አውቅልሽ፣
እኔ የጠየቁሽን ከመለስሽ፤
መስከረም ሲጠባ
አዲስ የጥብብ ቀሚስ ትሸለሚያለሽ።
ያን እውነት ንግግር
ተቀብየው በዚያ መንደር፤
በጋው አልፎ ክረምት መጥቶ
መስከረም ጠብቶ
ተጠይቄ እንቆቅልሽ
ለመፍታት ጉጉቴ ነበር፤
በዚያ የፍቅር መንደር።
ጥበብ ቀሚስ ለመሸለም
ምስክር የሚሆኑትም ነበሩ
ከብቶቹ፣ፍየሎቹ፤
አህያና በቁሎቹ።
በዚያ መንድር ስኖር
የለመለሙት ግራር፣
እንኮይና ወይራም
አልቀሩም በኔ ህልም፤
ምስክር እንዲሆኑ ቀሚሱን ስሸለም።
የልጅነት ጭውውት
አበቃና ተሻገርሁ ለቁም ነግር፤
በዚያ መንደር።
ወደ ጉልምስና
አሁንም መስከረም ሆነና
የሕይወት ምዕራፍ መክፈቻ አርሲ ሄድሁ
አዲስ ባህል አዲስ ሰውች ያልሰማሁት ቋንቋ
ለሃፍታም ለድሃ ተለይቶ
የሚያበላ አየሁ በዚያ
እኔም በድህነቴ ሳልሸማቀቅ
ካአብረኸትና ክትግሥት ጋር
ከላምቦረም ጭምር

ተወዳጀሁ በእምነት
በእህት አማችነት ተግባብተንም ነበር
ከላይ ከታች ስንዞር፤
ወረቀት አልነበረም የመታወቂያችን አርማ
ከኢትዮጵያዊነት በቀር።
ጊዜው ተገላብጦ
ምረጭ ተባልሁ
በጎሰኛው መንደር፤
አባቴ ከትግሪ
እናቴም ጎንደሪ
አክስቴ ሁለት ጊዜ አግብታ፤
ልጆቿ ናቸው ኦሮሞና ወላይታ።
ምን መጣና ነው አሁን የማይለወጥ
እንዲህ ያለ ሕገ ወጥ።
ጎሰኛውና መርዘኛው  ሞቷል
እስኪ አስቡና ተመለሱ
ወደ ህሊናችሁ፣
የተዘነቀ ጎሳችሁ፣
በገንዘብና በሙስናም የተዘፈቃችሁ፤
አላህም ሆነ ክርስቶስ ነው
አምላካችን ያላችሁ፣
ከጎሣ ይልቅ ይቅደም ሰባዊነታችሁ፤
እውነቱ ይህ ነው እኔ ልንገራችሁ።
በአውሮፓ ሆነ በአሜሪካ
ብትጓዙ ወይም ብትኖሩ
የሚያውቋችሁ መሆኑን ተገንዘቡ
እውነቱ ሳይሆን በጎሳችሁ፤
ነው በጥቁርነታችሁ።
ወደዳችሁም ጠላችሁም፤
ከቆዳችሁ አታመልጡም።
**ይልቅስ ተባብራችሁ፣**
**ፉከራ አሰሙ እባካችሁ፤**
**እንዲህ እያላችሁ።**
**አይደለም ጎሳ ማንነቴ፤**
**ለኔስ ይበልጥብኛል ሰውነቴ፣**
**በዚህ እምነቴም አትዳርጉኝ ለሞቴ።**

© ለምለም ፀጋው፣ 2015